

# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

**ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**

**የቀረበ የ2008 በጀት ዓመት የበጀት መግለጫ**


**ሱፊያን አህመድ**

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር**


**ሰኔ 2/2007 ዓ.ም.**

# Budget Speech

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 77 ተራ ቁጥር 3 የመንግስት በጀት በየዓመቱ እየተዘጋጀ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጸድቆ ሥራ ላይ መዋል እንደሚገባው ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሠረት በየዓመቱ እንደሚደረገው በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተደግፎ የቀረበውን የ2008 በጀት ዓመት ዓመታዊ የፌዴራል መንግስት በጀት ለተከበረው ምክር ቤት እንዲያፀድቀው ሳቀርብ ከፍተኛ ክብር ይሰማኛል፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

እንደሚታወቀው መንግሥትና ህብረተሰቡ በጋራ የነደፉትና የተከበረው ምክር ቤት ያፀደቀው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ትግበራ በያዝነው በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቅ ይታወቃል፡፡ የያዝነው በጀት ዓመት የዚህ ፓርላማ ዘመን የሚያበቃበትም ዓመት ነው፡፡ እንዲሁም የአምስተኛው ሀገራዊ ምርጫም በያዝነው በጀት ዓመት በተሳካ ሁኔታ የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሂደቱም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በኢትዮጵያ እየጎለበተ መምጣቱን ያሳየ እና ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ የታየበት ነበር፡፡ የቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ዕቅድም የሀገሪቱን ራዕይ በሚያሳካና እስከአሁን ተግባራዊ የተደረጉት ዕቅዶች ያስገኟቸውን የልማት ውጤቶች ዘላቂነት በሚያጠናክር መልክ ዝግጅቱ በዚሁ በጀት ዓመት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

**የተከበሩ አፈ ጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

ይህ ለ2008 በጀት ዓመት በምክር ቤቱ እንዲፀድቅ የቀረበው በጀትም በመዘጋጀት ላይ ባለው የቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ዕቅድ ላይ በመንግስት በጀት ተግባራዊ እንደሚደረጉ የሚጠበቁ ግቦችን ተፈጻሚ ለማድረግ በሚያስችል መንገድ የተዘጋጀ ነው፡፡ በመሆኑም የ2008 በጀት መግለጫን በዝርዝር ከማቅረቤ በፊት በዓምስት ዓመቱ የዕድገትና

ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በኢኮኖሚውና በልማቱ ረገድ የተገኙ አንኳር ስኬቶችንና ውጤቶችን ለተከበረው ምክር ቤት በአጭሩ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

ድህነትን ከሀገራችን ጨርሶ ለማጥፋትና መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ለማድረስ የተቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት በተያዘው ጎዳና ታላላቅ የልማት ግቦችን በመያዝ የተዘጋጀው የአምስት ዓመቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ተግባራዊ ምዕራፍ በያዝነው በጀት ዓመት ይጠናቀቃል፡፡ በአጠቃላይ ተግባራዊ ለማድረግ የተያዙ ዋና ዋና የኢኮኖሚና የልማት ግቦች አብዛኞቹን ማሳካት የተቻለበትና በሀገሪቱ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ የከፈቱ ታላላቅ የልማት ውጤቶች የተገኙበት እንደሆነ የዕቅዱ የእስከ አሁኑ ትግበራ ግምገማ አመልክቷል፡፡ ሆኖም በዕቅዱ ትግበራ በወጪ ምርቶቻችን የተቀመጡ ግቦች የተጠበቀውን ያህል የግብ ስኬት ያልተገኘባቸው ሆነዋል፡፡

እንደሚታወቀው የዕቅዱ ትግበራ ሙሉ ሪፖርት በተዘረጋው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መሠረት አፈጻጸሙ ተገምግሞ ለተከበረው ምክር ቤት የሚቀርብ ሲሆን፣ እስከ 2006 በጀት ዓመት የተከናወኑ ዋና ዋና የኢኮኖሚና የልማት ግብ ውጤቶችን ብቻ ለግንዛቤ ያህል አቀርባለሁ፡፡

በዚህም መሠረት ፈጣን፣ ዘላቂና መሠረተ ሰፊ የኢኮኖሚ ዕድገቱን ለማረጋገጥ የተያዘውን ግብ ከማሳካት አንጻር በመንግስት፣ በህብረተሰቡና በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከ2003-2006 ባሉት ዓመታት የአገራችን ኢኮኖሚ በአማካይ 10.1 በመቶ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ በዚሁ ጊዜ ውስጥ በግብርናው ዘርፍ በየዓመቱ በአማካይ 6.6 በመቶ ዕድገት የተመዘገበ ሲሆን፣ በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች በቅደም ተከተል የ20 በመቶ እና የ10.7 በመቶ አማካይ ዕድገት ተመዝግቧል፡፡ ይህ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት በዕቅዱ ከተቀመጠው ግብ አንጻርም ሆነ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት ከሚያስፈልገው የዕድገት መጠን እንዲሁም በሌሎች ፈጣን ዕድገት ከተመዘገበባቸው ሀገራት ኢኮኖሚ አንጻርም የተሳካ ግብ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያ እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት በሌሎች ከተመዘገቡ የኢኮኖሚ ዕድገቶች የተለየ የሚያደርገው ልዩ መገለጫው በዕቅዱ እንደተቀመጠው ፈጣን፣ ዘላቂ፣ መሠረተ-ሰፊ እና ፍትሀዊ የገቢ ክፍፍልን ያረጋገጠ

ዕድገት መሆኑ ነው፡፡ በአጠቃላይ በአራቱ ዓመታት የተመዘገበው ዕድገት በዕቅዱ በመሠረታዊ አማራጭ የተያዘውን የኢኮኖሚ ግብ ያሳካ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በእርግጥ የተመዘገበው ዕድገት በዕድገትና በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተቀመጠውን የኢኮኖሚ መዋቅር ሽግግር በዕቅዱ ከሚጠበቀው ግብ አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ማረጋገጥ ባይቻልም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከአጠቃላይ ኢኮኖሚው ያለው ድርሻ በ2003 ከነበረበት 10.3 በመቶ በ2006 ወደ 14.3 በመቶ በማደጉ መጠነኛ መሻሻል አምጥቷል፡፡ በዚህ ረገድ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ከኢኮኖሚው የሚኖረውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ቢሆንም በተለይ በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋና ውጤታማ ለውጥ ለማምጣት የተለየ ትኩረት መደረግ እንዳለበት ግምገማው ማሳየቱን ለመጠቆም እወዳለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በዕቅዱ የተገኘው የኢኮኖሚ ዕድገት መሠረተ ሰፊና በርካቶችን ተጠቃሚ ያደረገ በመሆኑ ባለፉት አምስት ዓመታት የዜጎች የገቢ አቅም እንዲሻሻል እና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አስችሏል፡፡ በተመዘገበው ፈጣን ዕድገት የዜጎች የነፍስ ወከፍ ገቢ (በጊዜው የገበያ ዋጋ) ያደገ ሲሆን፣ በ2003 ከነበረበት 396 የአሜሪካን ዶላር በ2006 ወደ 632 የአሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል፡፡ ይህም መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ለመሆን የያዝነውን ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል ነው፡፡ በዕቅዱ የትግበራ ዘመናት ተግባራዊ የተደረጉ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ለህብረተሰቡ በርካታ የሥራ ዕድሎች ፈጥረዋል፤ የህብረተሰቡንም ገቢ አቅም ማሳደግ አስችለዋል፡፡ በዚህም መሠረት በ1997 የድህነት ምጣኔው 38.7 በመቶ የነበረ ሲሆን፣ በ2003 ወደ 29.6 በመቶ ዝቅ ማለቱን የተደረገው በቤተሰብ ገቢና የፍጆታ ወጪ መረጃ ላይ ተመሥርቶ የተካሄደው የድህነት ዳሰሳ ጥናት አመላክቷል፡፡ ከ2004 ወዲህም በተከታታይ የተመዘገበው የኢኮኖሚ ዕድገት የድህነት ምጣኔው እንዲቀንስ ያስቻለ እንደነበረ ይታመናል፡፡ በያዝነው በ2007 ከሚመዘገበው ዕድገት ጋር በተያያዘ ከድህነት ወለል በላይ የሚሸጋገሩ ዜጎች ቁጥር ግምት ውስጥ ሲገባ ኢትዮጵያ ከድህነት ወለል በታች የሚገኘውን የህዝብ ቁጥር ምጣኔ በግማሽ ለመቀነስ ወይም 22.2 በመቶ ለማድረስ ያስቀመጠችውን የምዕተ ዓመቱን ግብ

ለማሳካት እንደቻለች ይገመታል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ባለፉት ዓመታት በተመዘገበው ዕድገት ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር የተቻለ ሲሆን በተለይም በከተሞች ውስጥ የነበረው ሥራ አጥነት ምጣኔ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ ሆኖም አሁንም ድህነቱና ሥራ አጥነቱ ከፍተኛ በመሆኑ በቀጣይ የኢኮኖሚ ዕድገቱን በማፋጠን የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ የማሻሻልና በሥራ ሥምሪት ያላቸው ተሳትፎ የማጠናከሩ ጉዳይ አሁንም ቅድሚያ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በአጠቃላይ ኢኮኖሚ ረገድ ሌላው የታየው የዕቅዱ አፈጻጸም የውጭ ንግድ አፈጻጸም ሲሆን፣ በዚህ ረገድ ከወጪ ምርቶች የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ሀገሪቱ ለገቢ ምርቶች የሚያስፈልጋትን ወጪ በውጭ ምንዛሬ የመሸፈን አቅም ለማሳደግ ጥረት መደረጉን መረዳት ይቻላል፡፡ የወጪ ምርቶችን በብዛትና በጥራት ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ ድጋፎች ተደርገዋል፡፡ በዚህም ምክንያት የኤክስፖርት ገቢ በዕቅዱ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ትግበራ ዓመታት ከፍተኛ ጭማሪ ማሳየት ችሏል፡፡ ሆኖም ከ2005 ጀምሮ የዕቃዎች ኤክስፖርት ዘርፍ አፈጻጸም በዚህ ደረጃ መቀጠል ባለመቻሉ የተገኘው የውጭ ምንዛሬ ገቢ ዕድገት ሳያሳይ እስከያዝነው በጀት ዓመት ድረስ በመዝለቁ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠው ከፍተኛ የኤክስፖርት ግብ ላይ መድረስ አለመቻሉን የተደረገው ግምገማ ያሳያል፡፡ በዚህ ዘርፍ ለታየው ደካማ አፈጻጸም አንዱ ምክንያት ወደ ውጭ የምንልካቸው ምርቶች ዋጋ በዓለም ገበያ መቀነስ ቢሆንም በዋነኛነት ግን ለውጭ ገበያ የምናቀርባቸውን የወጪ ምርቶች በዓይነት፣ በብዛት እና በጥራት የማቅረብ አቅማችን በሚፈለገው ደረጃ አለመዳበሩ ነው፡፡ የግብርና ምርታማነት እያደገ ቢመጣም የሚፈለገው ደረጃ ላይ አሁንም ገና አልደረሰም፡፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለመሠማራት ያለው ፍላጎት እያደገ ቢሆንም የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በማጠናከር የማኑፋክቸሪንግ ውጤቶችን ወይም አዳዲስ ምርቶችን በዓይነትና በብዛት በማምረት በስፋት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በቀጣይ ዓመታት የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ፣ በማኑፋክቸሪንግ መስክ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት፣ የኤክስፖርት ሸቀጦችን አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠንና በጥራት ማሻሻል እና የውጭ

ምንዛሬ ግኝትን ትርጉም ባለው ሁኔታ ማሳደግ በላቀ ትኩረት ርብርብ ሊደረግበት የሚገባ ተግባር መሆን እንደሚገባው ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በዕቅዱ ለተቀመጠው የኢኮኖሚ ዕድገት ግብ መሳካት አንዱና ወሳኝ ጉዳይ የኢንቨስትመንት መስፋፋት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ዕቅዱ ሰፋፊ ግቦችን ዕውን ለማድረግ የታለመ ከመሆኑ አንጻር የሚያስፈልገው የኢንቨስትመንት ፍላጎትና የፋይናንስ መጠን ከፍተኛ እንደነበረ የሚታወስ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የአገር ውስጥ ፋይናንስ አቅም እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረቶች የተደረጉ ሲሆን የውጭ ፋይናንስ ዕድልንም አቅም በፈቀደ ሁሉ ለመጠቀም ተሞክሯል፡፡ በተለይም ዜጎች መቆጠብ እንዲችሉ የፋይናንስ ተቋማት እንዲስፋፉ በማድረግና የተለያዩ የቁጠባ መሳሪያዎች ሥራ ላይ እንዲውሉና ዜጎችም የቁጠባ ትምህርት እንዲያገኙ የተደረገው ጥረት ሀገራዊ ቁጠባ በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድግ ረድቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ፍጥነት መስፋፋት መቻሉን የተገኘው የብሔራዊ ኢኮኖሚ አካውንት መረጃ አመልክቷል፡፡ በ2006 በጀት ዓመት የኢንቨስትመንት እና የሀገር ውስጥ ቁጠባ ምጣኔዎች በቅደም ተከተል 40.3 በመቶ እና 22.5 በመቶ በመድረስ በዕቅዱ ከተያዘው ግብ በላይ አፈጻጸም እንዲያሳዩ ማድረግ ተችሏል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የተገኘውን ውጤት በተለይም አሁን የተደረሰበትን የኢንቨስትመንት ምጣኔ በማስጠበቅ የቁጠባ ምጣኔያችን ግን የበለጠ እየተሻሻለ እንዲሄድ በማድረግ የኢንቨስትመንት ፍላጎታችንን በሀገር ውስጥ ፋይናንስ አቅም የመሸፈን አቅማችንን ማሻሻል ተገቢ ነው፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

እንደምናስታውሰው በዕቅዱ ትግበራ የመጀመሪያ ሁለት ዓመታት የዋጋ ዕድገት የዕቅዱ ፈታኝ ጉዳይ ሆኖ ነበር፡፡ ሆኖም ለዚህ መንግስት ጥብቅ የፊሲካል እና የገንዘብ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ በማድረግ የዋጋ ዕድገት በአንድ አሃዝ እንዲወሰን ማድረግ ተችሏል፡፡ ከዚህ ባሻገር በዕቅዱ የትግበራ ዓመታት በአመዛኙ ዕቅዱ ተግባራዊ ሲደረግ

የቆየው በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ የነበረ እንደሆነ መረዳት እንችላለን፡፡ በ2006 ደግሞ አማካይ የዋጋ ዕድገቱ 8.1 በመቶ ብቻ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለዘለቄታው የተረጋጋ ዋጋ እንዲኖር ለማድረግ በተለይም የምግብ ዋጋ ተረጋግቶ እንዲቀጥል የግብርና ምርታማነትን ማሳደግ፣ የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ማስፋፋት እና የአገር ውስጥ የግብይት ሥርዓቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ ወሳኝ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

በዕቅዱ ትግበራ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎችም በርካታ የልማት ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በዕቅዱ የተያዙ ግዙፍ የመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት አስተዳደርና የፋይናንስ አቅም በፈቀደው መጠን ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የመሠረታዊ አገልግሎቶችን ተደራሽነት ከማረጋገጥ አንጻርም በርካታ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

በዕቅዱ ትግበራ ዓመታት ሰፋፊ የመንገድ፣ የባቡር፣ የኢነርጂ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የውሃና የመሳሰሉ መሠረተ ልማት ዝርጋታዎችን ለማስፋፋት የታቀዱት አብዛኞዎቹ በርካታ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው መሠረት እስከያዝነው በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

ከነዚህም የመሠረተ ልማት ፕሮግራሞች መካከል ሀገራዊ የመንገድ ኔትዎርክ ለማስፋፋት ተግባራዊ የተደረጉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ የሀገሪቱ የመንገድ ሽፋን ከፍተኛ መሻሻል እንዲያሳይ አድርገዋል፡፡ የፌዴራልና የክልሎች መንገዶች ጠቅላላ የመንገድ ሽፋን በ2002 ከነበረበት 48,800 ኪ.ሜ. በ2006 ወደ 60,466 ኪ.ሜ. ከፍ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በሁሉን አቀፍ የገጠር መንገድ ተደራሽነት ፕሮግራም የተገነቡ የገጠር መንዶች ርዝመት በ2006 መጨረሻ 39 ሺህ ኪ.ሜ. የደረሰ ሲሆን ይኸም የአገሪቱ የመንገድ ርዝመት በድምር ወደ 100 ሺ ኪ.ሜ ከፍ እንዲል አስችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት ህብረተሰቡ ዋና ዋና መንገዶች ላይ

ለመድረስ የሚወስድበት ጊዜ በ2002 ከነበረበት 3.7 ሰዓት በ2006 ወደ 1.8 ሰዓት ዝቅ ብሏል። በባቡር ዝርጋታ ረገድ የተያዙም ፕሮጀክቶች አፈጻጸም እየተፋጠነ ይገኛል።

የኢነርጂ አቅርቦትን ለማስፋፋት ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ሲሆን የሀይል ማመንጨት አቅምን ለማሳደግ የሚያስችሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸምም በመልካም ደረጃ ላይ ይገኛል።

ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉና ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆኑ ከማድረግ አንጻር በርካታ ተግባራት ተከናውነዋል። በ2006 የመሰረታዊ የጤና አገልግሎት ሽፋን 100 በመቶ ለማድረስ የተቻለ ሲሆን የህብረተሰቡን የመሠረታዊ ጤና ሁኔታ ለማሻሻልና የህጻናትና የእናቶች ሞት ለመቀነስ አስችሏል። በተለይ በህጻናት ጤና ረገድ ሀገራችን የህጻናትን ሞት በሁለት ሦስተኛ ለመቀነስ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች የተቀመጠውን ግብ ከተቀመጠለት ጊዜ ሁለት ዓመታት ቀድማ ማሳካቷ የሚታወቅ ነው። በየአካባቢው እየተጠናከረ የመጣውን የህብረተሰብ ተሳትፎ በተለይም የሴቶች አደረጃጀቶች ተሳትፎ የእናቶችን ሞት ከመቀነስ አንጻር ትልቅ አዎንታዊ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ እየመጡ ያሉ ጅምር ውጤቶች አመላክተዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በትምህርት ዘርፍ የአንደኛ ደረጃ (1-8) ትምህርት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ጨምሮ ንጥር ተሳትፎ መጣኔ በ2006 በጀት ዓመት 92 በመቶ ደርሷል።

## የተከበሩ አፈ ጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

እንደሚታወቀው ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ዋና ዋና ስኬቶች የመንግስት ፊሲካል ፖሊሲ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር በመንግስት በኩል ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገር የተገኘውን የልማት ፋይናንስ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማስፋፋት በጀት በመመደብና በጀቱም ለታለመለት ዓላማ እንዲውል በመደረጉ ውጤቶች እንዲመዘገቡና የኢኮኖሚ ዕድገቱ እንዲፋጠን ማድረግ ተችሏል።

በዕቅዱ ትግበራ ዘመን ተግባራዊ የተደረገው የፊሲካል ፖሊሲ የታክስ ገቢን በማሳደግ እና በወጪ ረገድ የበጀት ድልድሉ በካፒታል ኢንቨስትመንት እና ድህነትን በመቀነስ ረገድ ቁልፍ ሚና ላላቸው ዘርፎች ቅድሚያ እንዲያገኙ በማድረግ ዓላማ ላይ

የተመሠረተ ነበር። በዕቅዱ ትግበራ ዘመን በሥራ ላይ ያለውን የታክስ አስተዳደር ሥርዓት ይበልጥ ማጠናከር ልማታችንን በአገር ውስጥ ገቢ የመሸፈን አቅማችን እንዲጎለብት ማድረግ ተችሏል። አብዛኛው የተገኘውም ሀብት ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው ለትምህርት፣ ለጤና፣ ለመንገድ፣ ለውሃና ለግብርና እንዲውል ተደርጓል። እንዲሁም የበጀት ጉድለቱ ለዋጋ አለመረጋጋት አስተዋጽኦ በማያደርግ መጠን እንዲገደብ የተደረገ ሲሆን ጥብቅ የፊሲካል ፖሊሲ ተግባራዊ ተደርጓል።

ይህም በመሆኑ በዕቅዱ የመጀመሪያ አራት ትግበራ ዓመታት የሃገር ውስጥ ገቢ በየዓመቱ በአማካይ በ29 በመቶ እያደገ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ። በተለይም የታክስ አሰባሰቡ 33 በመቶ ዓመታዊ አማካይ ዕድገት አሳይቷል። በ2006 በጀት ዓመት የተሰበሰበው ሀገራዊ የመንግስት ገቢና ዕርዳታ መጠን ብር 158 ቢሊዮን የነበረ ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ በበጀት ከታወጀው ዕቅድ አፈጻጸሙ 96.7 በመቶ ነበር። በ2006 የተሰበሰበው የታክስ ገቢ በአሃዝ ደረጃ በ2002 ከተሰበሰበው አንጻር ከሁለት እጥፍ በላይ ጭማሪ አሳይቷል። እንዲሁም ከታክስ ምንጭ የተሰበሰበው ገቢ የመንግስትን ወጪ የመሸፈን አቅሙም እያደገ የመጣ ሲሆን፣ ይህውም በ2006 በጀት ዓመት ከታክስ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበው ገቢ ከጠቅላላ የመንግስት ገቢ ውስጥ 84.2 በመቶ ድርሻ ሲይዝ፣ በ2003 69 በመቶ ነበር። እንዲሁም የታክስ ገቢው ከአጠቃላይ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መምጣት በ2006 የታክስ ገቢ ከጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት ያለው ድርሻ 12.7 በመቶ መድረሱን መረጃው ያሳያል። ሆኖም በዕቅዱ የተቀመጠውን የ15 በመቶ ግብ በያዝነው በጀት ለማሳካት አዳጋች እንደሚሆን መገመት አያስቸግርም።

በተመሳሳይ በወጪ ረገድ በዕቅዱ የትግበራ ዓመታት የመሠረተ ልማት ግንባታዎችና ድህነትን ለመቀነስ ቁልፍ ሚና ላላቸው ኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ልማት ዘርፎች የተመደበው ሀብት ከፍተኛውን ድርሻ የያዘ ሲሆን፣ በ2006 የአጠቃላይ ወጪውን 70 በመቶ የሚጠጋው ለነዚህ ዘርፎች ወጪ የተደረገ ነበር። ስለዚህም የመንግስት በጀት ሙሉ በሙሉ የልማትና የድህነት ቅነሳ በጀት ነው ብሎ መውሰድ የሚቻል ነው። እንዲሁም በአጠቃላይ ሲታይ በኢትዮጵያ በጀት አመዳደብ ለካፒታል በጀት ትልቁን ድርሻ የሚመደብበት ሲሆን፣ ይህም ከሌሎች በእድገት ደረጃቸው ከኢትዮጵያ ጋር ተቀራራቢና በማደግ ላይ ካሉ ሌሎች አገሮች ከሚታየው የሀብት አመዳደብ መርህ

አንፃር ሙሉ በሙሉ የተለየ ነው፡፡ በ2006 በጀት ዓመት በኢትዮጵያ የካፒታል በጀት ከጠቅላላው በጀት 58 በመቶ ሲይዝ መደበኛው ደግሞ 42 በመቶውን ይይዛል፣ ይህ በሌሎች አገሮች ከሚታየው አመዳደብ የተለየ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ መንግስት ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳይ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ያለፉት ዓመታት የዕቅድ አፈጻጸም ሲታይ በገቢ አሰባሰብም ሆነ በወጪ ድልድል በመልካም የአፈጻጸም ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የመንግስት ገቢና ወጪን በማመጣጠንና የበጀት ጉድለቱ የዋጋ ግሽበትን በማያስከትል ብድር እንዲሸፈን ማድረግ የተቻለበት ነው፡፡ በዚህም መሠረት የበጀት ጉድለቱ በዕቅዱ ከተቀመጠው በታች የነበረ ሲሆን የፊስካል ፖሊሲ አፈጻጸሙ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ
## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከዚህ በላይ እንደገለጽኩት ባለፉት በጀት □መታት ኢኮኖሚው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት እየተ□ዘ ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ አንዳንዶቹ ግቦች አስቀድመን የደረስንባቸው፣ አንዳንዶቹ ግቦች በያዝነው በጀት ዓመት የሚሳኩ መሆናቸውን የሚያመላክት አፈጻጸም ነው፡፡ አንዳንድ ያልተሳኩና ቀሪ ሥራዎች ደግሞ በቀጣዩ አምስት ዓመት ዕቅድ ተካተው ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የትግበራ ሂደት ትርጉም ያለው ተጨማሪ የማስፈጸም አቅም የተገነባ ሲሆን የተመዘገቡት ውጤቶችም በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ የልማት ተነሳሽነትና መነቃቃት ፈጥረዋል፡፡

የተከበሩ አፈጉባኤ

የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የያዝነው የ2007 በጀት ዓመት በመጠናቀቅ ላይ ቢሆንም ለበጀት ዓመቱ የተያዙ ዕቅዶች ስኬት በምን ደረጃ እንዳለ የሚያሳየው መረጃ በአብዛኛው በጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኃላ የሚገኝ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን፣ ከወዲሁ በሚታወቁ መረጃዎች ላይ ተመስርቶ ዕይታው ምን እንደሚመስል ለምክር ቤቱ መግለጽ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመጠናቀቅ ላይ ባለው የ2007 በጀት ዓመት የዕቅዱ ትግበራ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ ተግባራዊ የተደረገበት ዓመት ሲሆን፣ በርካታ ፕሮጀክቶች ወደ መጠናቀቅ የተቃረቡበት፣ በግብርናውም ረገድ ከፍተኛ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ሥራዎችና የግብርና ኤክስቴንሽንም በማስፋት ስትራቴጂው አማካኝነት ተጠናክሮ ተግባራዊ የተደረገበት በጀት ዓመት ነው፡፡ በበጀት ዓመቱ የመሠረተ ልማትና ማህበራዊ አገልግሎቶች የበለጠ የተስፋፉበት፣ ለልማታዊ ባለሃብቶች የሚደረገው እገዛም ተጠናክሮ የቀጠለበት፣ የሃገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ ሰፋፊ ሥራዎች በተጠናከረ ሁኔታ ተግባራዊ የተደረጉበት በመሆኑ የኢኮኖሚ ዕድገቱ ቀጣይነት ይረጋገጣል ተብሎ ተገምቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ እስከአሁን የተገኙት መረጃዎች እንዳሳዩትም ለኢኮኖሚው ዕድገት ከፍተኛ ድርሻ ባለው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ይመዘገባል ተብሎ የተቀመጠው ዕድገት እንደሚሳካ አሳይቷል፡፡ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በ2007 በጀት ዓመት በድምሩ 270.3 ሚሊዮን ኩንታል የመኸር ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ምርት ከአርሶ አደር እርሻ መሬት እንደሚሰበሰብ የጥናቱ ትንበያ አመልክቷል፡፡ ይህም በ2006 ከተሰበሰበው ተመሳሳይ የመኸር ምርት ጋር ሲወዳደር የ7.5 በመቶ ዕድገት እንደሚኖረው ያሳያል፡፡

የኢንዱስትሪ ዘርፍ የ2007 ትክክለኛ አፈጻጸም የሚያሳዩ መረጃዎች የሚደርሱት የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኂላ ቢሆንም በዘርፉ ከሚታየው እንቅስቃሴ አንፃር ኢንዱስትሪ በበጀት ዓመቱ እንደ አለፉት ዓመታት ሁሉ ፈጣን ዕድገት እንደሚያስመዘግብ ተገምቷል፡፡ ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከታቀፉት መካከል ዋነኞቹ የማኑፋክቸሪንግ እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡ በበጀት ዓመቱ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማረጋገጥ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በላቀ ፍጥነት እንዲያድግ ለማድረግ የወጡትን ስትራቴጂዎች በላቀ ደረጃ ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በዋናነት በግሉ ዘርፍ የሚከናወን እንደመሆኑ መጠን በዘርፉ

የሚደረገው የአገር ውስጥና የውጪ ኢንቨስትመንት ፍሰት በከፍተኛ መጠን እንዲጨምር ለማድረግ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው፡፡ የኢንዱስትሪውን ዕድገት ለመደገፍ ለግል ኢንቨስትመንት መስፋፋት ማነቆ ናቸው ተብለው የተለዩትን የመሬት አቅርቦት፣ የመንግስት አገልግሎት አሰጣጥና ፋሲሊቴሽን፣ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎት ችግሮችን ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም የማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ ተጠናክሮ ለኢንዱስትሪ ዕድገቱ የተሻለ አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል፡፡ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው በተለይም በመንግስት የሚካሄዱ ትልልቅ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ፣ ወጪና የጥራት ደረጃ እንዲጠናቀቁ ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ በመሆኑ በመልካም አፈጻጸም ደረጃ ላይ ይገኛሉ ብሎ መገመት ይቻላል፡፡ በግሉ ዘርፍ የሚካሄዱት የኮንስትራክሽን ሥራዎችም ቢሆን እንቅስቃሴያቸው በመልካም ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ስለዚህም የኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕድገትም ተስፋ የሚጣልበት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

በአገልግሎት ዘርፍ የታቀፉ ንዑስ ዘርፎችም በያዝነው በጀት ዓመት ዕድገት ማስመዝገብ እንደሚቀጥሉ ይጠበቃል፡፡ በአገልግሎት ክፍለ-ኢኮኖሚው ውስጥ የጅምላና ችርቻሮ፣ የፋይናንስ፣ የሪልኢስቴት፣ የመሳሪያ ኪራይና ተያያዥ ንግዶች፣ የትራንስፖርትና ኮሙኒኬሽን እንዲሁም የሆቴልና ሬስቶራንት የመሳሰሉት ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ለዘላቂ ዕድገቱ በጎ ሚና መጫወት እንዲችሉ ለማድረግ የወጡትን የንግድ ምዝገባ፣ ፈቃድ እና የአሠራር ህጎች በተሟላ ሁኔታ የሚደረገው ተፈፃሚነት ዘርፉን ይበልጥ ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ ዕድገቱ ቀጣይ እንደሚሆን ይታመናል፡፡ በመንግስት በኩል የሚካሄዱ የትምህርት፣ የጤናና የቴሌኮሙኒኬሽን የመሳሰሉት አገልግሎቶች ልማት በአስተማማኝ ሁኔታ ተግባራዊ እየተደረጉ በመሆናቸው ለ2007 በዕቅድ የተያዘውን ግብ በማሳካት ለአገልግሎት ዘርፉ የሚያደርጉትን የዕድገት አስተዋጽኦ ማሳካት እንደሚቻል ይታመናል፡፡

በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፎች እየታየ ካለው እንቅስቃሴ አንፃር ኢኮኖሚው በ2007 በጀት ዓመትም የ11.4 በመቶ ዕድገት እንደሚያስመዘግብ የሚያመላክቱ ሁኔታዎች መኖራቸውን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡

ሆኖም የኤክስፖርት ንግድ መቀዛቀዝ በያዝነው በጀት ዓመትም ከዘርፉ የሚጠበቀውን ግብ ለማሳካት የሚያስችል አፈጻጸም ያልታየበት መሆኑን ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡

በመሆኑም የሸቀጦች ኤክስፖርትን በሚመለከት ለበጀት ዓመቱም ሆነ በትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ የተያዘውን የዓምስት ዓመት ዕቅድ ለማሳካት የማያስችል አፈጻጸም እንደሆነ መረዳት ተገቢ ነው፡፡

በዋጋ ንረት አንጻር እስከአሁን ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ የተገኙት መረጃዎች እንዳሳዩት በያዝነው በጀት ዓመት የዋጋ ንረት በአንድ አሀዝ ዕድገት ተወስኖ እንደሚቀጥል የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በመንግስትበኩል በዋጋ ንረት የተገኘው ስኬት ቀጣይነቱ እንዲረጋጋጥ ትኩረት ተደርጎ ክትትል እየተደረገ በመሆኑ እንደአለፉት ዓመታት ለኢኮኖሚው አሳሳቢ ጉዳይ እንዳልሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በዚህም ረገድ ለበጀት ዓመቱ ተግባራዊ ለማድረግ የታቀዱትን የፊሲካልና ሞኒተሪ ፖሊሲ እርምጃዎች ትኩረት ሰጥቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ እንደሚገኝ ማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያዎቹ አሥር ወራት ከታክስና ታክስ ካልሆኑ ገቢዎች፣ የቀጥታ በጀት ድጋፍን ጨምሮ ብር 120.5 ቢሊዮን ገቢ ተሰብስቧል፡፡ ይህም ከፀደቀው የዓመቱ በጀት ጋር ሲነጻጸር 89.1 በመቶ አፈፃፀም አሳይቷል፡፡ በበጀት ዓመቱ አስር ወራት ዉስጥ ታክስ እና ታክስ ካልሆኑ ምንጮች የተሰበሰበው መደበኛ ገቢ ብር 117.6 ቢሊዮን ሲሆን ካለፈዉ በጀት ዓመት አፈጻጸም ጋር ሲነጻጸር የ23.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡ ከዚህ ውስጥም የተጣራ የፌዴራል መንግስት የታክስ ገቢ ብር 95.9 ቢሊዮን ሲሆን፣ የዓመታዊ ዕቅዱን 84.5 በመቶ ያህል መሰብሰብ መቻሉን ያሳያል፡፡ ይህ አፈጻጸም በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ በቀሪዎቹ ሁለት ወራት ቀሪውን ገቢ በመሰብሰብ በዕቅዱ የተያዘውን ብር 115 ቢሊዮን የታክስ ገቢ ዕቅድ ለማሳካት የሚቻልበት ሁኔታ እንዳለ ያመለክታል፡፡ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው አበረታች በሆነበት ሁኔታ በታክስ አስተዳደሩ በኩል ጠንካራ ርብርብ በማድረግ ቀሪውን ገቢ መሰብሰብ እንደሚቻል መገመት ይቻላል፡፡ ስለዚህም በዚህ ረገድ በታክስ አስተዳደሩ ረገድ ከፍተኛ ርብርብ ማድረግ እንደሚገባ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

በፊሲካል ፖሊሲ በኩል ወጪው በታቀደው መሠረት ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኝ ሲሆን የበጀት ጉድለቱም በዕቅድ ከተያዘው በታች እንደሆነና እየተሸፈነ የሚገኘውም የዋጋ ንረትን በማያስከትል ብድር እንደሆነ ላስገነዝብ እወዳለሁ፡፡

ስለዚህም በአጠቃላይ የ2007 በጀት ዓመት ከወጪ ምርቶች ኤክስፖርት አፈጻጸም መዳከም በስተቀር የኢኮኖሚው ዕይታ አዎንታዊ እንደሆነ ለማስገንዘብ እወዳለሁ፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የመንግስት ፋይናንስን ውጤታማና ቀልጣፋ ከማድረግ አንጻር፣ ዘመናዊ የፋይናንስ ሥርዓቶች እና ማሻሻያዎች ተዘርግተው ላለፉት በርካታ □መታት ተግባራዊ እ□ተ□ረቶ ሲሆኑ፣ በትግበራቸውም ውጤታማ የመንግስት ፋይናንስ ሥርዓት ከማረጋገጥ አንጻር ጉልህ ሚና እ□ተ□ □ቱ □ቆኖሉ:: በዚህም ኢትዮጵያ ጠንካራ የመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት ካላቸው ሀገራት መካከል አንዷ□እንድትሆን ዕገዛ ያደረገ ሲሆን፣ በአፈጻጸሙም ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎች እየታዩ ነው:: የማሻሻያው ሥራ አሁንም ተጠናክሮ ቀጥሏል::

በተጨማሪም የዋናው ኦዲተር ግኝቶች ላይ ክትትል በማድረግና የመንግስት ፋይናንስ አስተዳደር ይበልጥ ለማጠናከር ጥረት ተደርጓል፡፡ እስከ 2005 በጀት ዓመት ያለውን የዋናው ኦዲተር የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች የሂሣብ ምርመራ ግኝቶችን በተመለከተ የክትትልና የድጋፍ አሰጣጥ መርሃ-ግብር በማዘጋጀት፤ መ/ቤቶቹ በሁሉም ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወሰዱ በሰርኩላር በማሳወቅ፤ በባለበጀት መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች በአካል በመገኘት የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ድጋፍ በማድረግ፤ የዩኒቨርስቲዎች ኃላፊዎችን ጨምሮ የጋራ የምክክር መድረክ በማዘጋጀት፤ ለባለሙያዎቻቸውም በመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር ላይ ዝርዝር ሥልጠናዎችን በመስጠት ሰፊ ድጋፍ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በመንግሥት ግዥ እና የንብረት አስተዳደር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን የሚቀርፍ መመሪያና በተለይም ለዩኒቨርስቲዎች ደግሞ የተሻሻለ የውስጥ ገቢ አጠቃቀም መመሪያ በማዘጋጀት እንዲተገበሩ ተደርጓል፡፡

ከዚህም ሌላ የውስጥ ቁጥጥሩን ሥርዓት ለማጠናከር የየባለበጀት መ/ቤቶችንና የዩኒቨርስቲዎችን የመንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር፤ ግዥና ንብረት የውስጥ ኦዲትን ጨምሮ ከውጪ አገር ጭምር ጥናቶችን በማድረግ የአደረጃጀት ሰነዶች ተዘጋጅተው ወደ ትግበራ ለመግባት በሂደት ላይ ይገኛሉ፡፡

በሌላም በኩል የ2006 በጀት ዓመት የዋናው ኦዲት የምርመራ ሪፖርት ለምክር ቤቱ የቀረበው ባለፈው ሳምንት እንደመሆኑ መጠን ዝርዝሩን በመፈተሽ በቀጣይነት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚወሰዱ ይሆናል፡፡

በተጨማሪም የሀሪቱን የሂሳብና የኦዲት አፈጻጸም ሪፖርቶችን በሀገር ደረጃ ዓለም ዓቀፋዊና አንድ ወጥ አሠራር እንዲኖር ለማድረግ ባለፉት ዓመታት ጥናቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ በያዝነው በጀት ዓመት ይህንን የአሠራር ሥርዓት የሚያስፈጽም የኢትዮጵያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ መ/ቤት ተቋቁሞ ሥራውን ጀምሯል፡፡ የዚህ አሠራር በሀገራችን ተግባራዊ መደረግ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚኖረው ሲሆን፣ በተለይም የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ በዓለም ዓቀፍ የፋይናንስ ሪፖርት ስታንደርድ መሠረት እንዲሆን ማድረጉ በግሉ ዘርፍ ዓለም ዓቀፋዊ የሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ኢንዲኖር ያስችላል፡፡ ይህም የድርጅቶችን የውስጥ አሠራር ከማሻሻል በተጨማሪ አገራዊ የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምርና የመንግስት ገቢ አሰባሰብ እንዲሻሻል ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል፡፡ በመሆኑም ለትግበራው መፋጠን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

**የተከበሩ አፈጉባኤ**

**የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት**

ከዚህ ቀጥሎ የማቀርበው የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት በጀትን ለማዘጋጀት የተወሰዱ ዋና ዋና ታሳቢዎችንና ዝርዝር መግለጫዎችን ይሆናል፡፡ ከላይ በሪፖርቴ ለመግለጽ እንደሞከርኩት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ እንደሚያሳየው በርካታ ተግባራት በታቀደላቸው መሠረት ተግባራዊ የተደረጉ በመሆናቸው ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት የተመዘገበበት፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ውጤቶች የተገኙበት እንደሆነ አመልክቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ዕቅዱ በወሳኝነት የተሳካ ዕቅድ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ደግሞ ዘላቂና ፈጣን ዕድገቱን በማስቀጠል፣ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን በማረጋገጥ፣ በኢንዱስትሪ ልማትና የኤክስፖርት መስፋፋት ላይ አተኩሮ በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡ የዕቅዱ የትኩረት አቅጣጫም ዘላቂ የልማት ግቦችን እና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን ለማሳካት ተግባራዊ የሚደረጉ አንኳር ጉዳዮችን በተጠናከረ እንቅስቃሴ ተግባራዊ ማድረግ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በመንግስት በጀት ተግባራዊ የሚደረጉ ዕቅዶችም በበጀቱ ቅድሚያ በመስጠት ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናሉ፡፡ በመሆኑም ይህ የ2008 በጀት የቀጣዩን አምስት ዓመት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን

ዕቅድ ለማስፈጸም በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀነው። በዚህ ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀው የ2008 በጀት የሚከተሉትን ታሳቢዎችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

- ቀጣዩ የአምስት ዓመት ዕቅድ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘላቂ እድገትን የማስቀጠል እና የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን የማረጋገጥ ዓላማዎች ላይ ያተኮረ እንደሆን ታሳቢ ተደርጓል፣
- በ2008 በጀት ዓመት የ11.2 በመቶ የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት እንደሚመዘገብ ለበጀቱ እንደ አንድ ዋና ታሳቢ ተደርጎ ተወስዷል፣
- የዋጋ ዕድገት ሌላው የአጠቃላይ ኢኮኖሚ ታሳቢ ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት የ8 በመቶ አማካይ የዋጋ ዕድገት ታሳቢ ተደርጓል፣
- ሌላው ቀጣዩ የአምስት ዓመት ዕቅድ ታሳቢ በማኑፋክቸሪንግና በኤክስፖርት ዘርፍ የሚጠበቀው ከፍተኛ አፈጻጸም ሲሆን፣ ከዚህ በመነሳት የዕቃዎች ኤክስፖርት ገቢ እና የዕቃዎች ኢምፖርት ወጪ በቅደም ተከተል የ28.2 በመቶ እና የ21.6 በመቶ ዕድገት እንደሚያሳዩ ታሳቢ ተደርጓል፣
- የ2007 የታክስ ገቢ እስካሁን በታየው አፈጻጸም በመቀጠል ለበጀት ዓመቱ የተያዘውን ዕቅድ ለማሳካት የሚያስችል እንደሚሆን ለገቢ ትንበያው ታሳቢ ተደር□ል፣
- ለታክስ ገቢ ትንበያው በዋናነት የታክስ አስተዳደሩን ለማሻሻል ተግባራዊ የሚደረጉ የለውጥ ሥራዎች የታክስ ገቢ አሰባሰቡን ለማሻሻል የሚያስችሉ እንደሚሆን ከፍተኛ ግምት ተወስዷል፣
- ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች ምንጭ በዋናነት በመንግስት መ/ቤቶች ከሚሰጡ አገልግሎቶች ክፍያ፣ ከመንግስት ዕቃዎች ሽያጭ፣ ከመንግስት የልማት ድርጅቶች የዲቪደንድ ድርሻና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም ሌሎች ገቢዎች ላይ እንደሚሆን ግምት ተወስዷል፣
- የውጭ ሀብት ከፕሮጀክቶች ዕርዳታና ብድር እንዲሁም ከፒቢኤስ ዕርዳታና ብድር ምንጮች እንደሚገኝ፣ ከዚህ የሚገኘው ገቢ ከልማት አጋሮች በተገኘ መረጃ እና የፍሰቱን ታሪክ በማየት ግምት ተወስዷል፤
- መንግስት ለበጀት ጉድለት መሸፈኛ የሚወስደው ብድር የተቀመጠውን የገንዘብ ፖሊሲ ዓላማ በሚያሳካ እና የኢኮኖሚ ዕድገቱን በሚደግፍ ሁኔታ•እንደሚሆን ታሳቢ ተደርጓል።

የተከበሩ አፈጉባኤ

የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከላይ በዝርዝር በተቀመጡት ታሳቢዎች መሰረት በ2008 በጀት ዓመት ሊሰበሰብ የሚችለውን የገቢ ዕቅድና የወጪ በጀት እንደሚከተለው በዝርዝር አቀርባለሁ፡፡

የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢ ከሁሉም የገቢ አርዕስቶች ሊገኝ የሚችለውን የገቢ መጠን በዝርዝር በመገመት ተዘጋጅቷል፡፡ የ2008 የታክስ ገቢ ግምት መነሻ ያደረገው በ2007 እና ባለፉት ዓመታት ያለውን የታክስ ገቢ አፈጻጸም ግምት ውስጥ በማስገባት፣ በዕቅድ የተያዙ የታክስ አስተዳደር ማሻሻያ እርምጃዎች ተጠናክረው ተግባራዊ እንደሚደረጉና ለገቢ አሰባሰቡ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ታሳቢ በማድረግ እና የኢኮኖሚ ዕድገቱ የሚፈጥረውን የገቢ አቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተለይም የታክስ አስተምህሮት፣ የታክስ መረጃ ሥርዓት፣ እንዲሁም የታክስ አስተዳደሩ የክትትል እና የህግ ማስከበር ሥራ በተጠናከረ መንገድ ተግባራዊ መደረግና ውጤታማነት መሻሻል ለገቢ አሰባሰቡ ከፍተኛ ግምት ከተሰጣቸው ታሳቢዎች ዋናው ጉዳይ ነው፡፡

በዚህም ላይ በመመስረት የተገመተው የ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት አጠቃላይ ገቢ፣ የውጭ ብድርና ዕርዳታን ጨምሮ ብር 195,754,799,543 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከአገር ውስጥ ታክስና ታክስ ካልሆኑ የገቢ ምንጮች እንደሚሰበሰብ የተገመተው መጠን ብር 157,060,800,078 (80.2 በመቶ) እንደሚሆን ታቅዷል፡፡ ይህም የ2008 የአገር ውስጥ ገቢ ዕቅድ በ2007 በጀት ዓመት እንደሚሰበሰብ ከተገመተው ጋር ሲነጻጸር የ19.8 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በበጀት ዓመቱ ከታክስ ምንጭ ሊሰበሰብ የሚችለው ገቢ ብር 141,208,500,000 ሲሆን ከ2007 ክንውን ግምት ጋር ሲነጻጸር በ22.2 በመቶ ዕድገት ያሳያል፡፡ ታክስ ካልሆኑ ምንጮች (የካፒታል ገቢን ጨምሮ) ብር 15,852,300,078 ይሰበሰባል ተብሎ ተገምቷል፡፡

ከልማት አጋሮች በብድርና በዕርዳታ ይገኛል ተብሎ የተገመተው አጠቃላይ ገቢ ብር 38,693,999,465 ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 24,558,091,510 በብድር፣ እንዲሁም ብር 14,135,907,955 የሚሆነው ደግሞ በዕርዳታ መልክ የሚገኝ ነው፡፡ በቀጥታ ወደ መንግስት ትሬዠሪ ቋት ከሚገባው የመሰረታዊ አገልግሎቶች ድጋፍ ብር

6,676,272,000 በብድርና ዕርዳታ የሚገኝ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 1,074,372,000 የሚሆነው በዕርዳታ የሚገኝ ነው፡፡ ቀሪው ብር 5,601,900,000 ደግሞ በብድር መልክ ይገኛል ተብሎ የታቀደ ነው፡፡ ከጠቅላላ የውጭ ብድርና ዕርዳታ ውስጥ ብር 13,061,535,955 የሚሆነው በፕሮጀክቶች ዕርዳታ መልክ የሚገኝ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 18,956,191,510 ለፕሮጀክቶች የሚገኝ ብድር እንደሚሆን ተገምቷል፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የገቢ በጀቱ ከዚህ በላይ እንደቀረበው ሲሆን፣ የወጪ በጀት ድልድሉ በዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል፡፡ የፌዴራል መንግስት የ2008 የበጀት ዝግጅት መሠረት ያደረገው በመንግስት በመቀረጽ ላይ ካለው የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ቁልፍ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን አቅጣጫዎችና ዓላማዎችን፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀውን የመካከለኛ ዘመን የማክሮ ኢኮኖሚ እና ፊስካል ማዕቀፍን፣ እንዲሁም የማክሮኢኮኖሚ ታሳቢዎችንና ከአስፈጻሚ የመንግስት መ/ቤቶች ጋር የተደረገውን የበጀት ውይይት በግብዓትነት በመጠቀም ነው፡፡

በዚህም መሠረት ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከማስጀመር አንፃር፣ ከመንግስት የፋይናንስ አቅም፣ መ/ቤቶች ከተሰጣቸው ተልዕኮና ማንዴት አኳያ ለውጤቶች፣ ለዋና ዋና ተግባራትና ለፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን ወጪ በመገምገም በጀቱ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የፕሮግራም በጀት ሥርዓት በጀትን ከውጤት ጋር የሚያዛምድ የበጀት አሰራር ስርአት ሲሆን፣ ውጤትን ለመለካት፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ ፖሊሲና ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ እቅድን ከበጀት ጋር ለማስተሳሰር እና መደበኛና የካፒታል ወጪዎችን ለማቀናጀት የሚያስችል ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ ለ2008 የፕሮግራም በጀት ዝግጅት ታሳቢ የተደረጉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የ2008 በጀት ዓመት ረቂቅ በጀት የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP) እና የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችን (MDGs) በመተካት በዝግጅት ላይ

ያሉትን የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እና የዘላቂ የልማት ግቦችን (Sustainable Development Goals) ለመተግበር ታሳቢ በማድረግ፣

- ❖ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ለኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ ለኢንዱስትሪ ልማትና ለኤክስፖርት መስፋፋት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት ግምት ውስጥ በማስገባት፣
- ❖ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን የከፍተኛ ትምህርትን ከማስፋፋት አንፃር የተያዘውን ግብ ለማሳካት ሊገነቡ የታቀዱ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎችን ታሳቢ በማድረግ፣
- ❖ የተጀመረው የሲቪል ሰርቪስ የለውጥ ሰራዊት ግንባታ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ታሳቢ በማድረግ እና የሚገነባው የለውጥ ሰራዊት አስፈፃሚ መ/ቤቶችን ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ እንዲሆኑ እንደሚያስችላቸው ከግምት ውስጥ በማስገባት፣
- ❖ የሃብት ድልድሉን ለመምራት በሚያስችል መልኩ መ/ቤቶች አገራዊና የሴክተር እቅዶች ጋር የተሳሰረ የስትራቴጂክ እቅድ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ በጀት እንዲያዘጋጁ በማድረግ፤
- ❖ መ/ቤቶች በተመደበላቸው በጀት የሚያከናውኑት የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ለህብረተሰቡ የሚያስገኙት ውጤቶችና ለውጦች ግምት ውስጥ በማስገባት፣
- ❖ የመንግስት መ/ቤቶች የቀረጿቸው ፕሮግራሞች ከየመ/ቤቱ ተልዕኮና ማንዴት ጋር የተጣጣሙ እንደሚሆን ታሳቢ በማድረግ፤
- ❖ መ/ቤቶች ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጧቸውን አላማዎች እና ፕሮግራሞች በቅደም ተከተል እንዳቀረቡ ታሳቢ በማድረግ፤
- ❖ በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ታቅደው በካፒታል በጀት ሲከናወኑ የነበሩ ፕሮጀክቶች ተጠናቀው ወደ መደበኛ ስራ እንደሚገቡ ታሳቢ በማድረግ የመደበኛ በጀቱ ከፍ እንዲል በማድረግ፣
- ❖ የ2008 በጀት ዓመት የሁለተኛው የፕሮግራም በጀት ሳይክል (2007-2009) የሁለተኛ ዓመት እንደመሆኑ በ2007 በጀት ዓመት የታቀዱ ስራዎችን አፈፃፀም መሰረት በማድረግ የየፕሮግራሞቹን ውጤታማነት በመገምገም የ2008 በጀት ዓመት በጀት ከተቀመጠው ስትራቴጂክ ዓላማ፣ ግቦችና ከሚጠበቁ ውጤቶች አኳያ በመገምገም የፕሮግራም በጀት ተዘጋጅቷል፡፡

የተከበሩ አፈጉባኤ

የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን ዋና ዋና ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተዘጋጀው የ2008 በጀት ዓመት አጠቃላይ የፌዴራል መንግስት ወጪ በጀት ብር 223,397,819,261 ተደግፎ ቀርቧል፡፡ ይህ በጀት ተስተካክሎ ከጸደቀው የ2007 በጀት አንጻር የ19.7 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል፡፡

ከጠቅላላው የወጪ በጀት ውስጥ ብር 50,288,442,902 ለመደበኛ ወጪ፣ ብር 84,300,732,449 ለካፒታል ወጪ፣ ብር 76,808,643,910 ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ እና ብር 12,000,000,000 ለዘላቂ ልማት ግቦች (SDGs) ማጠናከሪያ ወጪዎች መሸፈኛ ተደግፎ የቀረበ በጀት ነው፡፡ ከዚህ ተደግፎ ከቀረበው የፌዴራል መንግስት ጠቅላላ የወጪ በጀት ውስጥ የካፒታል በጀት ድርሻ 37.7 በመቶ ሲሆን ከፍተኛውን ድርሻ ይዟል፡፡ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍ ድርሻ ደግሞ 34.4 በመቶ ሲሆን፣ የመደበኛ ወጪ በጀት እና የዘላቂ ልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪዎች በጀት ደግሞ በቅደም ተከተል የ22.5 እና 5.4 በመቶ ድርሻ ይዘዋል፡፡

ከፍተኛውን ድርሻ የያዘውን የካፒታል ወጪ በጀት ለመሸፈን የታቀደው ከአገር ውስጥ ከሚሰበሰብ ገቢና ከውጭ አገር በሚገኝ ዕርዳታና ብድር ሲሆን፣ ከመንግስት ትሬዠሪ፣ ከእርዳታ እና ከብድር በቅደም ተከተል ብር 56,241,564,284 (66.7 በመቶ)፣ ብር 12,413,656,955 (14.7 በመቶ) እና ብር 15,645,511,210 (18.6 በመቶ) ይይዛል፡፡

ከአጠቃላይ የ2008 መደበኛና ካፒታል በጀት ውስጥ 66.6 በመቶው የተመደበው ቅድሚያ ትኩረት ለተሰጣቸው የመንገድ፣ የትምህርት፣ የግብርና፣ የውሃ፣ የጤና እና የገጠር ኤሌክትሪፊኬሽን ፕሮግራሞች ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ረገድ ከፍተኛ ትርጉም ላላቸው የማኑፋክቸሪንግ፣ የኤክስፖርትና የከተማ ልማት ዘርፎች ከፍ ያለ በጀት በተጨማሪነት ተመድቧል፡፡ በመሆኑም በጀቱ ዘላቂ ልማት በማምጣት ድህነትን ለማስወገድ ቁልፍ ሚና ባላቸው ክፍላተ ኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት አውታሮችን በማስፋፋት፣ እንዲሁም የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን ለማረጋገጥ ላይ ያመዘነ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይህም

በሁለተኛው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተቀመጠውን የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንን አቅጣጫ በአግባቡ ለመተግበር እንደሚያስችል የሚያሳይ ነው፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ለሚያካሂዷቸው አጠቃላይ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች የሚያስፈልገው የወጪ ፍላጎት የሚሸፈነው በክልሎቹ ከሚሰበሰበው ገቢ እና በፌዴራል መንግስት በየዓመቱ በሚመደበው የበጀት ድጋፍ ነው፡፡ ይህ የበጀት ድጋፍ የክልሎችን ወጪ በመሸፈን ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ በመያዝ በሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚያዙ ግቦችን ለማሳካት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ በዚህም መሰረት ለ2008 በጀት ዓመት ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ብር 76,808,643,910 ወጪ በጀት ተደግፎ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከመንግስት ማዕከላዊ ቋት የተመደበው ብር 72,850,084,610፣ ከውጭ ፕሮጀክቶች ብድር ብር 3,310,680,300፣ እንዲሁም ከውጭ ፕሮጀክቶች ዕርዳታ ብር 647,879,000 እንደሚሆን ታቅዷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች (MDGs) በዘላቂ የልማት ግቦች (Sustainable Development Goals) የሚተኩ በመሆኑ በክልሎች የዘላቂ የልማት ግቦችን ለማጠናከር የሚያስችል ብር 12,000,000,000 በጀት ለ2008 በጀት ዓመት ተደግፎ ቀርቧል፡፡

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ከዚህ በላይ እንዳቀረብኩት በ2008 በጀት ዓመት የፌዴራል መንግስት ከሃገር ውስጥ የገቢ ምንጮች እንዲሁም ከውጭ አገር ዕርዳታና ብድር በድምሩ ብር 195,754,799,543 ገቢ እንደሚሰበሰብ በዕቅድ ተይዟል፡፡ እንዲሁም ለመደበኛ፣ ለካፒታል፣ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የበጀት ድጋፍና የዘላቂ የልማት ግቦች ማጠናከሪያ ወጪ ጠቅላላ ብር 223,397,819,261 በጀት ተደግፎ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሠረት በታቀደው የፌዴራል ገቢና ተደግፎ በቀረበው የወጪ በጀት መካከል የብር 27,643,019,718 የበጀት ጉድለት ይታያል፡፡ ይህንንም የበጀት ጉድለት ከሃገር ውስጥ

በሚገኝ ብድር ለመሸፈን ታቅዷል። የሀገር ውስጥ ብድር መጠኑ ከአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት አንጻር 1.8 በመቶ ብቻ በመሆኑ የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት ተግባራዊ ከሚደረገው የገንዘብ ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ ሲሆን በዋጋ ንረት ላይ ተፅዕኖ እንደማያሳድር ይታመናል።

## የተከበሩ አፈጉባኤ

## የተከበራችሁ የምክር ቤቱ አባላት

ለ2008 በጀት ዓመት የልማት ተግባራት ማስፈጸሚያ እንዲውል ተደግፎ የቀረበው የፌዴራል መንግስት በጀት ዝርዝር ከዚህ በላይ እንዳቀረብኩት ሲሆን፣ በጀቱ ለአገራችን የኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገት የሚያስፈልገውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ለተግባራዊነቱ መረባረብ እንደሚያስፈልግ ለተከበረው ም/ቤት እና ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ለማስገንዘብ እወዳለሁ። እንዲሁም የቀጣዩ አምስት ዓመታት ዕቅድ እስከአሁን የተገኘውን መልካም ውጤት በማስቀጠልና ድክመት በታየባቸው የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ከእስካሁኑ በበለጠ የሕብረተሰቡን ተሳትፎ ማጠናከርና ከፍተኛ ርብርብ እንዲኖር በማድረግ የበለጠ ስኬት እንዲኖር መረባረብ ይኖርብናል።

የልማት ዕቅዱን ለማስፈጸም እንቅፋት የሆኑብንን የማስፈጸም አቅም፣ የፋይናንስ ውስንነት፣ ዝቅተኛ የአገር ውስጥ ቁጠባ፣ ዝቅተኛ የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽን፣ የወጪ ንግድ መዳከም እና የመሳሰሉትን ዋና ዋና ማነቆዎች ለመፍታት የተጠናከረ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። ስለዚህም በጀቱን ካለፉት ዓመታት በተለየ መንፈስ ተፈጻሚ ለማድረግ ሁሉም የበኩሉን እንዲወጣ ጥሪዬን አስተላልፋለሁ።

ለ2008 ተደግፎ የቀረበው ይህ ረቂቅ የመንግስት በጀት ካለፉት ዓመታት በጀት ጋር ሲነጻጸር በጣም ከፍተኛ ነው። ለ2008 የያዝናቸውን የዘላቂ ልማትና ትራንስፎርሜሽን ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ሚናም ይኖረዋል። በመሆኑም ሁሉም ባለ በጀት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በቁጠባና በላቀ ውጤታማነት ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ለማሳሰብ እወዳለሁ። በተጨማሪም የሚጸድቀው በጀት የመንግስት የፋይናንስ፣ የግዥ እና የንብረት አስተዳደር ህግና ደንብ ብቻ ተከትለው ስራ ላይ እንዲያውሉ እያሳሰብኩ ይህንን ለማረጋገጥ እንዲቻል የሚደረገው የክትትልና የቁጥጥር ስራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ለመግለጽ እወዳለሁ።

በአጠቃላይ የ2008 በጀት ዓመት በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ እንዲሆን እየተመኘሁ፣ የበጀት ዝግጅቱ የተሳካ እንዲሆን የበጀት ጥያቄያቸውን በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳና በተዘጋጀው የበጀት ሥርዓት መሰረት ላቀረቡ አስፈጻሚ አካላት፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ በጀቱ ላይ ሰፊ ውይይት በማካሄድ በወቅቱ ለዚህ ምክር ቤት እንዲቀርብ በማድረጉ፣ ገቢ ሰብሳቢ ክፍሎችም ዝርዝር የገቢ ዕቅድ በማዘጋጀት እንዲሁም፣ የመገናኛ ብዙሐን ተቋማት የበጀት መረጃዎችን ለሕዝብ በማስተላለፍ ላደረጉት አስተዋጽኦ በመ/ቤቴና በምክር ቤቱ ስም ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም ይህን ተደግፎ የቀረበውን የ2008 ፕሮግራም በጀት የተከበረው ምክር ቤት እንዲያፀድቀው እጠይቃለሁ፡፡

**የኢኮኖሚ ትራንስፎርሜሽንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ**

**የኢትዮጵያ ህዳሴ ዕውን ይሆናል!!!**

**በጀት ለውጤት!!!**

**አመሰግናለሁ፡፡**